## የግል ተሽከርካሪዎች በልዩ መብት በቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ ወ ሀገር ስለሚገቡበት ሁኔታ የተሰጠው መብት ስለመሻሻሉ

## የወጣ መመሪያ ቁጥር 36/98

የጉምሩክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ታሪፍ ደንብ ቁጥር 122/85 ሁለተኛ መደ አንቀጽ (ለ) ንዑስ አንቀጽ 2(ለ) ለማሻሻል በወጣው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 6/88 አንቀጽ 2 መሠረት በውጭ አገ በኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን አገልግለው ወይም ለሌላ የመንግሥት ሥራ ለትምህርት፣ ለግል ሥራ በስደት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ውጭ ቆይተ የሚመለሱ ወይም መንግሥት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ መሠረት የሚመ ኢትዮጵያዊያን፣ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን እንዲሁም አካል ጉዳተኞች እ ተሸላሚ ኢትዮጵያዊያን የፌዴራል መንግሥት የገቢዎች ሚኒስቴር በአወጣቸ መመሪያዎች መሠረት የግል መገልገያ እና በሽልማት የተገኙ ዕቃዎቻቸውን ወ ሀገር ውስጥ በቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ እንዲያስገበ ሲደረግ ቆይቷል::

በተጠቀሱት መመሪያዎች ተሽከርካሪን በተመለከተ የተሰጡ መብቶችን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ የገቢዎች ሚኒስቴር በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 88/95 አንቀጽ 3 እና በደንብ ቁጥር 6/88(እንደተሻሻለ) አንቀጽ ለ(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል::

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ በልዩ መብት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 36/98 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. ማሻሻያ

   2.1 በልዩ መብት ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥ እና ታክስ ክፍያ የግል መገልገያ ዕቃዎች ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጡት የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያዎች ቁጥር 7/1996፣ 22/1997 እና 29/1998 እንደሚከተለው ተሻሽለዋል:

መለሰ ፈንታ
ሚኒስትር

በመመሪያዎቹ፡-

- በኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን አገልግለው ለሚመለሱ፣
- በተለያዩ የኢትዮጵያ መንግሥት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች አገልግለው ለሚመለሱ፣
- ለኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ባህርተኞች፣
- በአሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶች ውስጥ ሲያገለግሉ ቆይተው ለሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ፣
- በትምህርት ውጭ ቆይተው ለሚመለሱ፣
- በስደት ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ ቆይተው ጠቅልለው ለሚመለሱ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን፣
- ለአካል ጉዳተኞች፣
- መንግሥት በሚያደርገው ልዩ ጥሪ ለሚመጡ ባለሙያዎች እና
- የቅጥርና የሥራ ውል አድርገው ለሚመጡ ባለሙያዎች

ተሰጥቶ የነበረው፣ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወይም በቀረጥና ታክስ ክፍያ የግል ተሽከርካሪን የማስገባት ፈቃድ በዚህ መመሪያ ተነስቷል::

2.2 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2.1 የተደነገገው ቢኖርም

- በኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን፣
- በተለያዩ የኢትዮጵያ መንግሥት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች፣
- የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ባሕርተኞችና
- በአሕጉራዊና አለም አቀፋዊ ድርጅቶች ውስጥ ሦስት ዓመትና ከዚያ በላይ ሲያገለግሉ ቆይተው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያን አንድ የግል አውቶሞቢል ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ::

2.3 በተመሳሳይ ሁኔታም በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ አገር አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ ቆይተው ጠቅልለው ወደአገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን አንድ የግል አውቶሞቢል ቀረጥና ታክስ በመክፈል ማስገባት ይችላሉ::

2.4 የሽልማት ዕቃዎች ወደ አገር ስለሚገቡበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣው የገቢዎች ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 23/1997 እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሠርዞ ማንኛውም ሰው በውጭ አገር በታወቁ የዓለምና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች አገርንና ሕዝብን ወክሎ ወይም በግል በውድድር በመካፈል ባገኘው የብልጫ ውጤት መሠረት ከተሸከርካሪ በስተቀር ማናቸውንም የሽልማት ዕቃዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ክፍያ በነፃ ወደ ሀገር ያስገባል:: በሽልማት የተገኘው ተሽከርካሪ ከሆነ ለአንድ ጊዜ ብቻ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባል:: ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገባ፣ ለሁለተኛ እና ከዚያ በላይ ተሽከርካሪን በሽልማት ካገኘ በቀረጥና ታክስ ክፍያ ያስገባል በሚል ተስተካክሏል::

2.5 ለአካል ጉዳተኞች የሚያገለግሉ ልዩ ዕቃዎችና መሣሪያዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ስለሚገቡበት ሁኔታ ግንቦት 15 ቀን 1994 ዓ.ም. በቁጥር 01/72/64/6 የወጣው መመሪያ እንደሚከተለው ተሻሽሏል::

2.5.1 በመመሪያው በተለያዩ አንቀጾች "አካለስንኩል" በሚል የተገለጸው "የአካል ጉዳተኛ" በሚል ተስተካክሏል::

2.5.2 የመመሪያው አንቀጽ 3 ተሠርዞ ከዚህ በሚከተለው ተተክቷል::

ማንኛውም የአካል ጉዳተኛ ለተጐዳው አካሉ ቀጥተኛ ድጋፍ የሚሰጡ ከመኪና በስተቀር ልዩ ዕቃዎችንና መሣሪያዎችን ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል::

3. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

3.1 ይህ መመሪያ ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል::

3.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ከፀናበት ዕለት አስቀድሞ ወደ ሀገር ለመግባት በተጫኑ፣ በመንገዝ ላይ በሚገኙና ለጉምሩክ ሥነ ሥርዓት አፈፃፀም በቀረቡ የግል አውቶሞቢሎች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ክፍል
Ministry of Revenues Records and Documentation

መላኩ ፈንታ
ሚኒስትር